# አስተያየት በሦስት ጉዳዮች ላይ

(አብዱራህማን አህመዲን፤ የቀድሞ የፓርላማ አባል)
**Email: ahayder2000@gmail.com**

***(ይህ ጽሑፍ ቅጽ 2፣ ቁጥር 29፣ ጥር 10 ቀን 2006 ዓ.ም በወጣው ፋክት መጽሔት ላይ ታትሟል። መጽሔቱን የማያገኙ፣ በተለይም በውጭ ሀገር ያሉ ዜጎች ሁሉ ቢያነቡት 'ይጠቅማል' በሚል መንፈስ በድረ-ገጽ ላይ እንዲታተም ተልኳል።)***

ይህንን ጽሑፍ እንዳዘጋጅ ምክንያት የሆነኝ በፋክት መጽሔት ቅጽ 2፣ ቁጥር 26 የታህሳስ ወር 2006 እትም ላይ በፕሮፌሰር መስፍን፣ በጋዜጠኛ ተመስገን ደሣለኝ እና በአቶ አስራት አብርሃ የቀረቡ ሦስት መጣጥፎች ናቸው። ሦስቱም ሰዎች ባቀረቧቸው ሃሳቦች ላይ ያለኝን አስተያየት አጠር አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

## 1. የአቶ ኃ/ማሪያም "እብሪቅ"

በወሎ አማርኛ "እብሪቅ" ማለት፤ የውሃ መያዣ ማንቆርቆሪያ ወይም በራድ ማለት ነው። የአካባቢው የእስልምና እምነት መምህራን (ሼህዎች) ለ'ዑዱ' ውሃ መያዣነት የሚጠቀሙበት ሲሆን፤ ለተለያዩ ጉዳዮች ከቦታ ቦታ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት አንድ ወይም ሁለት (አንዳንድ ጊዜ ከዚያም በላይ) ደረሳዎች (ተማሪዎች) የሼህአቸውን "እብሪቅ" ይዘው ከኋላ ኋላ ይከተላሉ። ሼሁ ውሃ ለመጠጣትም ይሁን 'ዑዱ' ለማድረግ (ለመታጠብ) ሲፈልጉ ደረሳዎቹ እብሪቁን ያቀብላሉ።

መቼም ወሎ ላይ ሳቅ ጨዋታ፣ ዋዛ ፈዛዛ ሞልቷል። እና ይህንን ሁኔታ ያስተዋሉ አንዳንድ ጨዋታ አድማቂዎች፤ ሁለት በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ሰዎች አንድ ላይ ሲሄዱ ያዩ እንደሆነ "እንቶኔ የእከሌ እብሪቅ ሆኗል" በማለት ሳቅ ጨዋታ (Fun) ይፈጥራሉ። አንዱ ከአጠገባቸው ተነስቶ ሲሄድ ሌላው ልከተል ያለ እንደሆነ ደግሞ "ምነው እብሪቅ መሆን አማረህ እንዴ?" በማለት ተረብ መሳይ ቀልድ ጣል ያደርጋሉ።

ይህንን ሃሳብ የጽሑፌ መንደርደሪያ ያደረግኩት ያለ ምክንያት አደለም። ከላይ ቀንና ቁጥሩን በገለጽኩት የመጽሔቱ እትም ላይ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም ባቀረቡት ጽሑፍ "ሻምበል ጉታ ዲንቃ ከጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማሪያም ጋር ለማንዴላ ቀብር ወደ ደቡብ አፍሪካ መሄድ ነበረባቸው" ማለታቸውን ሳነብ ነው የ"እብሪቅ" ነገር ትዝ ያለኝ።

ሀገሮች እና የየሀገራቱ መሪዎች የሚኖራቸውን ግንኙነት የሚመሩበት "ፕሮቶኮል" የተሰኘ የተጻፈም ያልተጻፈም ሕግ እና እንደ ሕግ የሚቆጠር ልማዳዊ አሰራር መኖሩን ፕሮፌሰር መስፍን በእድሜ መግፋት ዘንግተውት ከሆነ ላስታውሳቸው እወዳለሁ። የኢትዮጵያ መንግስትም የሚመራው በዚሁ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባለው የአሰራር ደንብና ስርዓት እንደሚሆን እገነዘባለሁ። ከዚህም የዓለም "ስርዓት" በመነሳት፤ እነፕሮፌሰር መስፍን አባል የሆኑበት ፓርቲ (ፓርቲያቸው ቅንጅት ይሁን አንድነት፣ ሰሚያዊ ይሁን መርህ ይከበር አልለየሁትም) ስልጣን ቢይዝና (አያድርግባቸውና) ፕሮፌሰር መስፍን ጠቅላይ ሚኒስትር ቢሆኑ እንኳ፤ 'ሻምበል ጉታ ከእርሳቸው ጋር አብረው ሊሄዱ አችሉም' ብሎ፣ አፍን ሞልቶ ያለ ምንም ጥረጥር መናገር ይቻላል። በዚህም ምክንያት ነው የፕሮፌሰር መስፍን ሃሳብ ማስተዋል ያልታከለበት ሆኖ የታየኝ።

እንዲያው ለነገሩ ሻምበል ጉታ ከጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማሪያም ጋር “እብሪቅ” ሆነው በመሄዳቸው ለሀገሪቱም ሆነ ለግለሰቡ የሚያስገኘው ፋይዳ ምንድነው? የሻምበል ጉታ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር አለመሄድ ‘አገሪቱን የሚመሩት ሰዎች ለሀገር የማያስቡ’ መሆናቸውን ማረጋገጫ መስፈርት መሆን የሚችለውስ በየትኛው ሥነ-አመክንዮ (Logic) ነው? ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፕሮፌሰር መስፍን የሚናገሩት ወይም የሚጽፉት ነገር ከአስተማሪነቱ ይልቅ አስቂኝነቱ እያመዘነ መምጣቱን አስተውያለሁ። ማንዴላ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ (ከሃያ ዓመታት በላይ) ምንም ነገር ትንፍሽ ያላሉት ሻምበል ጉታ ሰውየው ከሞቱ በኋላ በየሚዲያው ነገሩ እንዲጋጋል ማድረጋቸው ለምን እንደሆነም ባወጣ ባወርድ ሊገባኝ አልቻለም።

ፕሮፌሰር መስፍን ያነሱትን 2ሺህ ፓውንድ በተመለከተም ሻምበል ጉታ በወቅቱ አምነውበት ያደረጉት እስከሆነ ድረስ በፀፀት ከንፈር የሚያስመጥጥ ሆኖ አይታየኝም። ለነገሩ ሻምበሉ በተዋናይነት የሚሳተፉበት ፊልም በመሰራት ላይ መሆኑ እየተነገረ ስለሆነ፤ ሁሉንም የሚያካክስ ክፍያ እንደሚያገኙ መገመት ይቻላል።

ስለሆነም፤ ፕሮፌሰር መስፍን በመጣጥፋቸው ያነሱት ሃሳብ በየትኛውም መመዘኛ ጽሑፉን ለማዘጋጀት ያባከኑትን ጊዜ፣ ጉልበት፣ ወረቀትና ቀለም ያህል ዋጋ ያለው ሆኖ አላገኘሁትም። ስንት ሊጻፍበት የሚገባ ሀገራዊ አጀንዳ እያለ በእንደዚያ ዓይነት ተራ ነገር ላይ ጊዜና ጉልበት ማባከን ከክሽፈትም በላይ ክሽፈት ከመሆን የዘለለ ትርጉምም ፋይዳም አይኖረውም ባይ ነኝ።

## 2. የተመስገን አብዮቶች

ጋዜጠኛ ተመስገን ደሣለኝ ከፍትህ ጋዜጣ እስከ ፋክት መጽሔት ድረስ በተለያዩ ጊዜአት ያቀረባቸውን የተለያዩ መጣጥፎች የተወሰኑትን አንብቤአለሁ። ወንድሜ ተመስገን “ደፋር” ብእር እንዳለው አስተውያለሁ። የብዕሩን “ደፋርነት” አደንቃለሁ። በ“ደፋር” ብእሩ በሚያነሳቸው አንዳንድ ‘በድፍረት የተሞሉ’ ሃሳቦቹ ላይ ግን አልስማማም። ከማልስማማባቸው ሃሳቦቹ አንዱና ዋነኛው በ“አብዮት” ዙሪያ የሚያነሳው ጉዳይ ነው።

እኔና ተመስገን ብዙ የእድሜ ርቀት ያለን አይመስለኝም። የአንድ ትውልድ ሰዎች እንደሆንን አስባለሁ። ልጅ እና ወጣት ሆነን ሀገሪቱ ያስተናገደቻቸውን ሁለት አብዮቶች (የ1966ቱን እና የ1983ቱን) ያየን ይመስለኛል። በበኩሌ የ1966ቱን የአምስት ዓመት ልጅ ሆኜ፣ የ1983ቱን የሃያ ሁለት ዓመት ወጣት ሆኜ አይቻለሁ።

ከዓይን እማኝነቱ ሌላ የሌሎች ሀገሮችን አብዮቶች በተመለከተም በበቂ ሁኔታ አንብቤአለሁ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስ እማር በነበረበትም ወቅት ስለ ማህበራዊ አብዮት (Social Revolution) ምንነት፣ አነሳስ፣ ሂደትና ውጤት ወዘተ. አንድ ሰፋ ያለ ኮርስ ወስጃለሁ። እናም አብዮትን በተመለከተ የጠራ ግንዛቤ እንዳለኝ አምናለሁ።

ከዚህ ሁሉ ግንዛቤዬ በመነሳት ኢትዮጵያ ሀገራችን ሦስተኛ አብዮት ያስፈልጋታል ወይ? ካለፉት ሁለት “አብዮቶች” ያገኘነው ጥቅምና ጉዳት ምንድነው? ሁለቱ አብዮቶች በቂ ምላሽ ያልሰጡት የሕዝብ (የማኅበረሰብ) ጥያቄስ የቱ ነው? የሕዝብ (የማኅበረሰብ) ጥያቄ አለ ከተባለስ ያ ጥያቄ መመለስ ያለበት ምድር በሚያንቀጠቅጥ አብዮት ነው ወይስ በሰላማዊ መንገድ? ወዘተረፈ የሚሉትን ጥያቄዎች ደግሜ ደጋግሜ በማንሳት በአእምሮየ አብሰለስላለሁ። ለመሆኑ አብዮት ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን አምጦ የመውለጃ መንገድ ነው? የሚል ተጨማሪ ጥያቄም እንዲሁ በአእምሮዬ ነፍስ ዘርቶ ሲላወስ ይሰማኛል።

በኔ እምነት የአንድ ሀገር የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ በሆነ የታሪክ አጋጣሚ (በሰላማዊ ወይም ሰላማዊ ባልሆነ መንገድ) ሊጀመር ይችላል፡፡ በብዙ ሀገሮች እንደታየው፤ እንከን የለሽ፣ ምሉዕ፣ ሕዝብን ከጫፍ እስከ ጫፍ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚያደርግ የዴሞክራሲ ስርዓት በአንድ ጊዜ ሊመሰረት አይችልም፡፡ የእነ አሜሪካ ዴሞክራሲ ከሞላ ጎደል በተግባር ላይ ዋለ ሊባል የሚችለው ከ200 ዓመታት በኂላ መሆኑን ነው ተመራማሪዎች የሚነግሩን፡፡ ይሄ ማለት ግን እኛ የዚያን ያህል ጊዜ ያስፈልገናል ማለት አደለም፡፡

ከእነ አፍላጦን (Plato) እና አሪስጣጣሊስ (Aristotle) ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በዘርፉ የተሰማሩ የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪዎች የሚያስተምሩትም ዴሞክራሲ ሂደት (Process) መሆኑን ነው፡፡ በዚህ አባባል መስማማት የምንችል ከሆነ፤ ጉዳዩን ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማነጻጸር መመርመር የሚጠበቅብን ይመስለኛል፡፡ በኔ ግምት የምርምራችን ውጤት ሊሆን የሚችለው ሁለት ነው፡፡ አንድም አሁን ያለውን የ"ዴሞክራሲ ጅማሮ" ማጠናከር፣ አሊያም ጅማሮው ተስፋ አስቆራጭ ስለሆነ እሱን ትቶ ሌላ 'ሦስተኛ አብዮት' ማካሄድ!

ወንድሜ ተመስገን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ስለ "አብዮት አስፈላጊነት" የሚያወሱ መጣጥፎችን በተደጋጋሚ የሚያስነብበን (እንደ ምሁር) በመጀመሪያ ደረጃ አሁን ያለውን የሀገራችንን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሂደት በተመለከተ ተገቢውን ጥናትና ምርምር በማድረግ ባገኘው ውጤት ላይ በመመስረት ከሆነ ጥሩ ነው፡፡ ያ ከሆነ ደግሞ ሁላችንም ሃሳቡን ለመጋራት እንችል ዘንድ በቅድሚያ የጥናቱን ውጤት አቅርቦ ብንወያይበት መልካም ነው፡፡ ከዚያ በኂላ የሚኖረው ክርክር በእውቀትና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ስለሚሆን ተግባብቶ በጋራ ለመስራትም ይሁን በልዩነት ለመኖር ተመራጩና የሰለጠነው መንገድ ይኸው ይመስለኛል፡፡

በአብዮት ጉዳይ ላይ ስሜትን በመግለጽ ረገድ እኔም እንደ ተመስገን ስሜቴንና ፍላጎቴን ለመግለጽ ብዙ ምርምር ሳያስፈልገኝ አሁን ባለኝ እውቀትና ግንዛቤ ላይ ተመስርቼ ለመግለጽ የሚገደኝ አይመስለኝም፡፡ በእውቀትና በመረጃ ላይ ተመስርቶ ትንታኔ ያልተደረገበት ተራ ስሜት ግን ገዢ ሆኖ ብዙዎችን ሊያስማማ እንደማይችል አስባለሁ፡፡ እንደኔ እንደኔ "አብዮት ማካሄድ" ቀርቶ "አብዮት" የሚለውን ቃል ባልሰማ እመርጣለሁ፡፡ "አብዮት" ወንድም ወንድሙን/እህቱን ገድሎ የሚፎክርበት የጅል መንገድ መሆኑን አምናለሁና!!!

ሀገራችን የረጅም ዘመን የአስተዳደር ታሪክ እንዳላት ቢታወቅም፤ በረጅም የሀገርነት ታሪኳ የተደራጀና ከትውልድ ወደ ትውልድ የተሸጋገረ ሀገራዊ መዋቅርም ሆነ የአስተዳደርና የአሰራር ስርዓት አልነበራትም፤ የላትምም፡፡ የሩቁን ዘመን ትተን የቅርቡን እንኳ ብናይ፤ ሀገራችን "በሕገ-መንግስት" መተዳደር ከጀመረች ሰማንያ ዓመታት ገደማ የተቆጠሩ ቢሆንም፣ ቀደም ሲል የነበሩት ሕገ መንግስቶች አርቅቀው በስራ ላይ ያዋሉዋቸው መንግስታት ሲቀያየሩ እየተቀደዱ በመጣላቸው በሕገ መንግስት መሰረት የተቋቋመ፣ ቀጣይነት ያለው አደረጃጀት ሊኖረን አልቻለም፡፡ ዘመን ተሻጋሪ መዋቅር ሊኖር ባለመቻሉም ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት የሚያስችሉ፣ በየጊዜው የሚሻሻሉ አስተዳደራዊ፣ የፍትሕና የሲቪል ሰርቪስ መዋቅር የለንም፡፡

እንደሚታወቀው አሁን በስራ ላይ ያለው ሕገ መንግስት በስራ ላይ ከዋለ 19 ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም፤ ሀገሪቱ በዚህ ሕገ መንግስት መሰረት ተሰርታ አልተጠናቀቀችም፡፡ በዚህም ምክንያት ለአንድ ሀገርና ሕዝብ የሚያስፈልጉት የዴሞክራሲ ስርዓት ማረጋገጫ ተቋማት፣ አደረጃጀትም ሆነ የአሰራር ስርዓት በቅጡ አለን ለማለት አያስደፍርም፡፡ ይህ ተጨባጭ እውነታ ባለበት ሁኔታ ሦስተኛ "አብዮት" እናካሂድ የምንል ከሆነ አሁን ያለው ሕገ መንግስት ተቀዶ ይጣላል፣ አሁን ባለው ሕገ መንግስት መሰረት ተቋቁመው ዳዴ እያሉ ያሉ አደረጃጀቶች ይፈርሳሉ፣ አሁን ባለው ሕገ መንግስት መሰረት የተመሰረተው መንግስት ይፈርሳል፣

የተጀመረው የምርጫ ሥርዓት ይቋረጣል፣… ከዚያ በኋላ ደግሞ አዲስ የሽግግር መንግስት ይመሰረታል፣ ሌላ ሕገ መንግስት ይጻፋል፣ በዚያ ህገ መንግስት መሰረት ምርጫ ተደርጎ መንግስት ይመሰረታል፣… ወዘተ. ማለት ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ (Back to Square one!) ከመሆን የዘለለ ትርጉምም ፋይዳም የለውም፡፡ በዚህ ዓይነት አካሄድ የምንቀጥል ከሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ እኛ እናውቅልሃለን ከሚሉ የፖለቲካ ልሂቃን ልጆቹ መጫወቻነት ሊገላገል አይችልም ማለት ነው፡፡ እንግዲህ እነ ተመስገን (“እነ” ያልኩት የተመስገንን ሃሳብ የሚደግፉ ሰዎች እንዳሉ በማሰብ ነው) እያመላከቱን ያለው እንዲህ ያለ ውጤት የሚያስከትለውን ጠመዝማዛ መንገድ መስሎ ነው እየታየኝ ያለው፡፡

በኔ እምነት የሚሻለንም የሚበጀንም በውሃ ቅዳ ውሃ መልስ መንገድ መንጎድ ሳይሆን፤ አሁን ባለው ሕገ መንግስት መሰረት እየተመራን ያሉትን ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የማይበጁ ክፍተቶች መፈተሽ፣ ማሻሻል፣ ማረምና ማስተካከል ብቻ ነው፡፡ ይህ አካሄድ ረጅም ጊዜ መጠየቁና እልህ አስጨራሽ መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ ውጤቱ ግን እንኳን በእኛ ምናልባትም በቀጣዩ ትውልድም በተሟላ ሁኔታ ላይታይ ይችላል፡፡ ዴሞክራሲ በባህሪው አቋራጭ መንገድ የሌለው በመሆኑ እየመረረንም፣ እየጎመዘዘንም ሀቁን ከመቀበል ውጪ አማራጭ ሊኖረን አይችልም፡፡

ይሁን እንጂ፣ ረጅም ጊዜ ቢወስድም የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት “ላብን” እንጂ “ደምን” የሚጠይቅ ባለመሆኑ ውጤቱ የሕሊና እረፍትን ያጎናጽፋል፡፡ እናም፤ አሁን ያለው ትውልድ “አብዮት” ማካሄድ ሳይሆን ባለው ላይ አዎንታዊ ተደማሪ (Positive Incremental) ሥራ በመስራት ረጅሙን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ጉዞ ማሳጠር ይጠበቅበታል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ሁላችንም በሰከነ መንፈስ ካየነው የአብዮት ሂደትም ሆነ ውጤት አጥፊ ነው፡፡ ጥቂቶች በሰሩት ስህተት ዛሬ ሀገሪቱን የተሻለ ደረጃ ሊያደርስ የሚችል አንድ ትውልድ የአብዮት እሳት በልቶት ዶግ አመድ ሆኗል፡፡ አብዮት በብእር ሲጽፉት ቀለል ብሎ ሊታይ ይችል ይሆናል፡፡ በእንግሊዝኛው “Revolution” እና “Civil Disobedience” የሚሉት ጽንሰ ሀሳቦች ፍፁም የተለያዩ ናቸው፡፡ ተመስገን ስለ “Civil Disobedience” እየነገረን ከሆነም አቀራረቡንም ቋንቋውንም ያስተካክል፡፡

እናስ ወንድሜ ተመስገን የትኛው መንገድ ነው የሚሻለን ትላለህ? መልስህን እንደ ፖለቲከኛ ሳይሆን እንደ ጋዜጠኛ አስበህ ብትነግረን አይከፋም፡፡ እንዲህ ያልኩበት ምክንያት፤ ፖለቲከኛ እነ ማኪያቬሊ “The end justifies the means” እንደሚሉት “የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው” የሚል መፈክር አንግቦ ቢነጉድ፤ “ዓላማው በተገኘው መንገድ የስልጣን መንበር ላይ ቂብ ማለት ስለሆነ ስህተት ተደርጎ ሊታይ አይገባም” የሚል መከራከሪያ ማንሳት ስለሚቻልና ጋዜጠኛ ግን ዓላማው ስልጣን ላይ መውጣት ሳይሆን ብዙሃኑን (ከተቻለ ሁሉንም) የሚጠቅም ሂደትና ውጤት እንዲገኝ ማድረግ ስለሆነ፤ ሚዛኑን የጠበቀ ሃሳብ የማቅረብ የሙያና የህሊና ግዴታ አለበት የሚል እምነት ስላለኝ ነው፡፡

## 3. “ቁማርተኞች” የሌሉበት አማራጭ

የወንድሜን የአስራት አብርሃን መጣጥፍ አነበብኩት፡፡ አስራትን ያስጨነቀው የፓርቲዎች ውህደት በሚፈለገው ፍጥነት ተራምዶ ፍጻሜ ሳያገኝ በሰበብ አስባቡ እየተገነባ መተርተሩ ነው፡፡ ለዚህም ተጠያቂዎቹ “ቁማርተኛ” የሆኑት የፖለቲካ ልሂቃን ናቸው ባይ ነው፡፡ የአስራትን መጽሐፍም ሆነ አንዳንድ መጣጥፎቹን አልፎ አልፎ አንብቤአለሁ፡፡ አስራት ጥሩ

“ሀገር ወዳድ” መሆኑ ይታየኛል፡፡ ይኸው አገር ወዳድነቱ ፋታ ነስቶ፣ ወደ ፖለቲካው ጎትቶ ያስገባውም ይመስለኛል፡፡ በሀገር ጉዳይ ላይ የዳር ተመልካች፣ በታሪክም ፊት ተጠያቂ ከመሆን ሁሉንም ነገር ገብቶ ማየቱ መልካም ነው፡፡ በመግባቱም እነሆ የሀገሪቱን “ቀንደኛ የፖለቲካ ቁማርተኞች” ማንነት በቅርብ ርቀት ለማየት የቻለ ይመስለኛል፡፡

አስራት ይህንን መጣጥፍ ያዘጋጀው “የፖለቲካ ቁማርተኞቹን” ማንነትና ፍላጎት ካጤነ በኋላ በመሆኑ በውስጡ የሚንበለበለው ቁጭት፣ ስጋትና ምኞት አካል ገዝፎ፣ ነፍስ ዘርቶ ሲንቀሳቀስ በእዝነ ህሊናዬ ይታየኛል፡፡ ወንድሜ አስራት በጽሑፉ በገለጻቸው ሃሳቦችና ትንተናዎች ከሞላ ጎደል እስማማለሁ፡፡ በትንተናው የምስማማው ያነሳቸው ሀሳቦች ትክክለኛና ተጨባጭ ስለሆኑ ብቻ አደለም፡፡ ይልቁኑ ሀሳቡን ከጥላቻ በራቀ መንፈስ ለማቅረብ ያደረገውን ጥረት በመረዳቴ ጭምር ነው፡፡ በኔ እምነት አንድ ፖለቲከኛ “ምሉእ ነው” ሊባል የሚችለው ከጥላቻ የራቀ እንደሆነ ነው፡፡ ጥላቻን በውስጡ አጭቆ ይዞ ‘ለሕዝብ መብትና ጥቅም ቆሜአለሁ’ የሚል ፖለቲከኛ እሱ የቁም ሞት የሞተ ተላላ ነው፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አስራት በመጣጥፉ ውስጥ ያላካተታቸው ሁለት ነጥቦች የቀሩ ስለመሰለኝ ነው ይህቺን ማስታወሻ ለመክተብ የተነሳሁት፡፡ ይኸውም፤ አንደኛ በተቃዋሚው ጎራ እንደ ተራራ ገዝፎ የሚታየውን “አግላይ” የፖለቲካ አካሄድ በትንተናው ውስጥ ትኩረት አልሰጠውም ባይ ነኝ፡፡ በኔ እምነት በተቃዋሚው ጎራ እስከ ዛሬ ድረስ እየተገነቡ ለፈረሱት ውህደቶች አንዱና ዋነኛው ምክንያት ውህደቱ በመርህ የማይመራ፣ ገና ከጅምሩ የተወሰኑትን አግልሎ የተወኑትን አቅፎ የሚንቀሳቀስ መሆኑ ነው፡፡ መድረክም ገና ከጥንስሱ ይህንኑ የውድቀት መንገድ ነበር የተከተለው፡፡

የፖለቲካ ሳይንስ ጠቢባን “ፖለቲካ ተለዋዋጭ (Dynamic) ነው፡፡ እናም በፖለቲካ ዘላለማዊ ጠላትም ይሁን ዘላለማዊ ወዳጅ የለም (There is no eternal enemy and eternal friendship in politics)” ይላሉ፡፡ መድረክ ከዚህ መርህ በማፈንገጥ “የውህደቱ በር ለእነ እከሌ ክፍት ነው፣ ለእነ እንቶኔ ዝግነው” በሚል መንፈስ ሥራውን ጀመረ፡፡ እኔ እንደማስታውሰው የመድረክ የውህደት እንቅስቃሴ “ሀቀኛ ተቃዋሚዎች” በሚል ቋንቋ ላይ የተንጠለጠለ ነበር፡፡ የመድረክ መስራቾች እንደዚያ ዓይነቱን አገላለጽ የተጠቀሙት እነማንን ለማመላከት እንደሆነ “እንኳን ይቺን የዝንብ ጠንጋራ እናውቃለን” ለሚሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች የተሰወረ አልነበረም፡፡

የመድረክን “ሀቀኛ ተቃዋሚዎች” የሚል አካሄድ ሰንካላና አግላይ የሚያሰኘው የሚከተሉትን ወጣሪ ጥያቄዎች ስለሚቀሰቅስ ነው፡፡ ጥያቄዎቹም፤ ሀቀኛ የሆኑትና ያልሆኑት ፓርቲዎች የትኞቹ ናቸው? የሀቀኛነት መመዘኛ መስፈርቱ፣ መለኪያ ሚዛኑ ምንድነው? መስፈርቱን ያወጣውስ ማን ነው? መስፈርቱን ለማውጣት ማን ስልጣን ሰጠው? በመስፈርቶቹ ላይ ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች መክረዋል? ተስማምተዋል? እና ባልተስማሙበት መስፈርት መስፈርስ ይቻላል? ውጤቱስ ተቀባይነት ይኖረዋል?....?...?

እነዚህ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ሳያገኙ የመድረክ ሰዎች ራሳቸው መስፈርት አውጪ፣ ራሳቸው መዛኝ፣ ራሳቸው ውጤት ሰጪ፣... ሆኑና ተጠራርተው በመቧደን “ድርጅት መሰረትን” ብለውን አረፉት! ይህም አካሄድ የውህደቱን ሂደት አግላይ አደረገው፡፡ እናም የአስራት ትንተና እነዚህን ሁኔታዎች በአግባቡ አላካተተም የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡ ይህ ደግሞ አስራት የሚጓጓለትን ውህደት ጎደሎ የሚያደርገው ይመስለኛል፡፡

አስራት በመጣጥፉ አላካተተውም የምለው ሁለተኛው ነገር፤ ለተቃዋሚው ጎራ መጠናከር ከውህደት ሌላ አማራጭ የሌለ አስመስሎ ማቅረቡን ነው፡፡ የተቃዋሚውን ጎራ ጠንካራ

ተፎካካሪ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ውህደት መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ ሀቀኛ ውህደት ሊፈጠር ያልቻለው በተቃዋሚው ጎራ ያሉ አንዳንድ የፓርቲ መሪዎችና የፖለቲካ ልሂቃን የውህደት ቁማርተኛ በመሆናቸው መሆኑን፣ በዚህም ምክንያት የመድረክ ውህደት ሊሳካ አለመቻሉን፣ የመድረክ ውህደት መጓተት ሲታይበት አንድነትና አረና የውህደት እንቅስቃሴ መጀመራቸውን፣ ይህ እንቅስቃሴ ፍጻሜ ሳያገኝ አንድነት ከመኢአድ ጋር አረና ደግሞ ከደቡብ ሕብረት ጋር ሌላ የውህደት እንቅስቃሴ መጀመራቸውንና ይህም ለውጤት እንደማይበቃ፣… ይተርክልናል አስራት፡፡ የፖለቲካውን የኃይል አሰላለፍ ሊለውጥ የሚችለውና የተቃዋሚዎችን ጥንካሬ ሊያመጣ የሚችለው ውህደት ብቻ መሆኑንም ይነግረናል አስራት፡፡

በኔ እምነት ውህደት የተቃዋሚውን ጎራ እንዲጠናከር የሚያደርግ አንዱ መንገድ እንጂ ብቸኛው አማራጭ አደለም፡፡ እናም፤ ተቃዋሚዎች ተዋህደውና ተጠናክረው መውጣት ካልቻሉ ምን መደረግ አለበት? ተብሎ ሌሎች አማራጮች መፈተሽ አለባቸው፡፡ በበኩሌ ከውህደት ውጪ ሌላ አማራጭ ይታየኛል፡፡ ይኸውም፤ እስከዛሬ የተሞከሩ የውህደት እንቅስቃሴዎች ሊሳኩ ያልቻሉት "በመሪነት ደረጃ ላይ ባሉት 'የዚያ ትውልድ' ልሂቃን ምክንያት ነው" ከተባለ፣ መፍትሄው ነባሮቹን ፓርቲዎች እርግፍ አድርጎ ለዚያ ትውልድ አባላት መተውና በአዲሱ ትወልድ አመራር ሰጪነትና የነቃ ተሳትፎ የተገነባ አዲስ ፓርቲ ማቋቋም ነው፡፡ ነገሩ ሁሉ ታጥቦ ጭቃ እንዳይሆንና ኢዴፓን መስርተው የነበሩት ወጣቶች አመራሩን ለታላላቆቻቸው "የዚያ ትውልድ" ሰዎች በመስጠታቸው የሰሩት ዓይነት ስህተት እንዳይደገም የቀዳሚው ትውልድ አባላት በአዲሱ ፓርቲ ውስጥ የሚኖራቸው ሚና "ከተራ አባልነትና ከመካከለኛ አመራርነት እንዳያልፍ የሚያደርግ መርህ" መከተልም አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሰሚያዊ ፓርቲ ውስጥ የሚስተዋሉ በጎ ነገሮች ቢኖሩም፤ አንዳንድ "ቀንድ መንከስ" የሚቃጣቸው ችኩል አመራሮች ሲካለቡ ፓርቲውን በአፍ-ጢሙ ደፍተውት ተያይዘው ዘብጥያ እንዳይወርዱ ያሰጋል፡፡ ማንን እንደሚታገሉና ትግሉ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ከስሜት ወጥተው በቅጡ ያሰቡበት አልመሰለኝም፡፡

ለኔ የሚታየኝ መፍትሄ ይሄ ነው፣ ያዋጣል የሚል እምነትም አለኝ፡፡ አዲሱ ፓርቲ የሁሉንም ብሔር፣ ብሔረሰቦች ጥያቄዎች ያነገበ፣ ማህበራዊ መሰረቱን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ አደረጃጀቱ በተቻለ መጠን ሕብረ ብሔራዊ ገጽታን የተላበሰ እንዲሆን በርትቶ መስራት ነው፡፡ አቶ አስራት! ውህደት ምናምን እያላችሁ ድሪቶ በመጣፍ ከምትደክሙና ጊዜ ከምታባክኑ "ጥቂቶች ቁራጦች" ይሄኛውን መንገድ እስኪ ጀምሩት!